# የሳኦል ፍሬዎች ፊልም ተመረቀ

በኖርዌይ በርገን ከተማ በቢከስ አዳራሽ ማርች 28 ቀን 2015 ዓ.ም በዓይነቱ የመጀመሪያ የሆነ 'የሳኦል ፍሬዎች' በሚል ርዕስ በበርገን ቅርጫፍ የኢሳት ድጋፍ ሰጪ ኮሚቴ አስተባባሪነት የተዘጋጀው ፊልም በርካታ እንግዶች በተገኙበት ተመረቀ።

በእለቱ ዝግጅቱን የመሩት በበርገን ቅርጫፍ የኢሳት ድጋፍ ሰጪ ህዝብ ግንኙነት አቶ ዳዊት እያዩ የፊልሙ ምርቃት ዝግጅት መጀመሩን አብሰረው በፊልሙ ምርቃት ላይ ከአመስተርዳም ጋዜጠኛ እና አርቲስት ገሊላ መኮንን ፣ ከበርገን የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ ሊቀመንበር አቶ ተስፋዬ ኮርፊል እንዲሁም ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች እንዲሁም የበርገን ነዋሪዎች ፣ በፊልሙ የተሳተፉና ተጋባዥ አርቲስቶች ተገኝተዋል።

በበርገን ቅርጫፍ የኢሳት ድጋፍ ሰጪ ኮሚቴ ሊቀመንብር የሆኑት አቶ ሰለሞን አሸናፊ እና ጋዜጠኛ ገሊላ መኮንን በአዳራሹ ውስጥ ለተገኙት እንግዶች የእንኳን ደህና መጣችሁ መልዕክት አስተላልፈዋል ፡፡ እንዲሁም በዚህ በውጪው አለም ብዙም ያልተሞከረው " የሳኦል ፍሬዎች " ፊልም ለተመልካች ቀርቧል ፡፡



ከዚህ በመቀጠል የሳኦል ፍሬዎች ፊልሙ ላይ ወደ በርገን አመጣጡን ፣ የተዋንያኑን መረጣ ፣ ከጥናቱ ጀምሮ እስከ ፊልም ቀረጻው ስላከናወናቸው ውጣ ውረዶች ቀረጻው የፈጀውን የግዜ ርዝመት ፣ የሰው ሃይል ብዛት እና ፊልሙን እስኪጠናቀቅ ድረስ የነበረውን ውጣ ውረድ ጠቅለል አድርገው ገለጻ ያደረጉት የበርገን ቅርጫፍ ኢሳት ድጋፍ ሰጪ ሊቀመንበር አቶ ሰለሞን አሸናፊ ሲሆኑ በቀጣይ በፊልሙ ላይ ተዋናይ እና ዳይሬክተር ስክሪፕት ሪ ራይተር የሆነችው ለፊልሙ ሙያዊ እገዛ በማድረግ ፊልሙ ተጀምሮ እስኪያበቃ ድረስ ከጎናችን በመሆን ፣ በፊልሙ ስራ ላይ አብላጫውን ቦታ ይዛ የምትገኘው ፡ ሙሉ የፊልሙን ቀረጻ በመውሰድ አሰልቺውን እና አድካሚውን የኤዲቲንግ ስራ ከባለሙያቹ ጎን ሳትለይ ፣ ለመጀመሪያ ግዜ ፊልሙ መመረቅ ያለበት በተሰራበት ቦታ በኖርዌይ በርገን ከተማ ነው በማለት ይህን እድል የሰጠችን ጋዜጠኛ እና ተዋንያን ገሊላ መኮንን የዚህ ፊልም የኔ ድርሻ ከአንዳርጋቸው ጽጌ ከጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ ከጀግኖቹ ጀርባ ላሉት ሴቶች እህቶቼ ይሁንልኝ በማለት ፊልሙ ስላሳለፈው ሁኔታ ገለጻ አድርጋለች ፡፡

ለሳኦል ፍሬዎች ደራሲና ተዋንያን አይንሸት ገበያው ካሳ ምንም እንኳ በእለቱ በዝግጅቱ ላይ ባይገኝም ፊልሙን የተመለከቱት እንግዶች ለደራሲና ተዋንያን አይንሸት ገበየሁ ወቅታዊ ሁኔታን የሚያሳውቅ፣ አርዓያና ምሳሌ የሚሆን ፊልም ነው በማለት በመደነቅ ሞቅ ያለ አድናቆትና ጭብጨባ ችረውታል ፡፡

የበርገን ቅርጫፍ ኢሳት ድጋፍ ሰጪ ኮሚቴ ከዛሬ 4 ወር በፊት ባሳወቀው ኢሳት ይቀጥላል መርህ መሰረት ሁሉም የህብረተሰብ ክፍሎች ከሚያደርጉት ድጋፍ ጎን ለጎን እኛም የአቅማችንን ለመወጣት በተሰራው በዚህ በሳአል ፍሬዎች ፊልም በአንድ ድንጋይ ሁለት ወፍ መተንበታል ብለዋል ፡፡

1. ይህ ፊልም ከምረቃው በሃላ ኢሳት በሚደርስባቸው ቦታዎች ሁሉ ፣ በአውሮፓ እንዲሁም በአሜሪካ በሁሉም የኢሳት ቤተሰቦች ባሉበት ቦታ ሁሉ በሚያዝለት የግዜ ሰሌዳ መሰረት ለእይታ ይቀርባል ከዚህ ከሚያገኘው ገቢ በሃገራችን ላይ በመረጃ እጥረት በወያኔ የሃሰት ማታለያ እየተጨብረበረ ላለው ወገናችን ኢሳት የህዝባችን አይንና ጆሮ ሆኖ እንዲቀጥል የኢኮኖሚ ድጋፍ በመሆን ያገለግላል እንዲሁም በኢሳት ቴሌዚዠን ይተላለፋል በተጨማሪም ከእይታ ሲወርድ በቪሲዲና በዲቪዲ ተባዝቶ ለህዝቡ ለሽያጭ ይቀርባል ፡፡
2. በወያኔ እየደረሰብን የሚገኘውን አፈና ግድያ ስደት የህዝባችንን በደል በተወሰነ መልኩ አሳይተንበታል ይህ ፊልም የመጀመሪው በመሆን ብዙ የተደበቁ እውነተኛ ታሪኮችን መሰረት ያደረጉ ሌሎች ፊልሞችም እንዲሰሩ መነሻ ይሆናል ፡፡

በአጠቃላይ በዚህ ደረጃውን ጠብቆ በተሰራው ፊልም ላይ ለተሳተፉ የውዲቷ ሃገራችን ልጆች ከኢሳት ማኔጅመንት እና ከበርገን ቅርጫፍ የኢሳት ድጋፍ ሰጪ ኮሚቴ የተዘጋጀላቸውን አበባ የምስክር ወረቀት እና የምስጋና ደብዳቤ ፣ አዘጋጁ ኮሚቴ በ 3 ክፍል ከፍሎ ሰጥቷቸዋል ፡፡

በምረቃው ላይ ከተገኙ ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች መካከል ለ3ቱ ስጦታውን የሰጡልን በበርገን ቅርጫፍ የኢሳት ድጋፍ ሰጪ ሊቀመንበር አቶ ሰለሞን አሸናፊ ሲሆኑ

በአንደኛ መደብ ተሸላሚ ደራሲና ተዋንያን የፊልሙ መሰረት መነሻ የሆነው ወጣት ደራሲ አቶ አይንሸት ገበያው ካሳ / ተፈሪን ሆኖ የተወነው / ሲሆን ምንም እንኳ በእለቱ ባይገኝም በተወካይ በኩል ስጦታው ተሰጥቶታል ፡፡ ሁለተኛዋ ተሸላሚ ፊልሙ ደረጃውን ጠብቆ እንዲሰራ ፣ የፊልሙን ድርሰት ሪ ራይት እና ዳይሬክት በማድረግ ሙያዊ እገዛ ስታደርግ የነበረችው ጋዜጠኛ አርቲስት ገሊላ መኮንን ነበረች ፡፡ በሶስተኛ ደረጃ ተሸላሚ የነበረው ይህ ፊልም ለታሪክ እንዲተላልፍ ከንብረቱ ከሙያው በተጨማሪ ከሳአል ፍሬዎች ደራሲ ጋር በመነጋገር ለኮሚቴው ሃሳቡን ይዞት የመጣው እንዲሁም በተዋንያን መረጣ ሰፊውን ድርሻ ወስዶ ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይል የቀረጻውን ስራ ሲያከናውን የነበረው ካሜራ ማን አቶ ቶማስ አለባቸው ነበሩ ፡፡

በሁለተኛ መደብ ተሸላሚ የነበሩት መሪ ተዋንያኑ ሲሆን ስጦታውን የሰጡልን በበርገን የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ ሊቀ መንበር አቶ ተስፋዬ ኮርፊል ነበሩ ፣ የመጀመሪያው ተሸላሚ በፊልሙ ላይ ዋናውን ገጸ ባህርይ ወክሎ የተወነው ወጣት መክብብ ሙሉጌታ ( ሃይሉን ሆኖ የተወነው) ሲሆን ሁለተኛው ተሸላሚ ለፊልሙ ማማር የራሱን ድርሻ በሚገባ የተወነው አቶ ሳሙኤል ተወልደ ( መሃሪ) በሶስተኛ ተሸላሚ አቶ አንተነህ አማረ (ወዲ ጠቆ) በአራተኛ ተሸላሚ የሴቶችን ተሳትፎ በማሰደግ ላይ የምትገኘው ወ/ሪት ሜሮን አድማሱ (ማስተዋል) በመሆን ስጦታቸውን ተቀብለዋል ፡፡

በሦስተኛ መደብ ተሸላሚ የነበሩትን ተዋንያን ስጦታው የሰጡልን በበርገን ነዋሪ የሆኑት በሃገራዊ እና ማህበራዊ ጉዳዮች ላይ ሁሌም ከወገናቸው ጎን በመቆም የሚታወቁት ወ/ሮ ምስራቅ ነበሩ ፡፡ የመጀመሪያው ተሸላሚ አቶ ብሩክ ጌታነህ (ዋሴን ሆኖ የተወነው ) ሁለተኛው ተሸላሚ አቶ ሰለሞን አሸናፊ (ቦጋለን ሆኖ የተወነው) ሦስተኛዋ ተሸላሚ ከነቤተሰብዋ ወ/ሮ ሰላም በጋሻው (የመሰረት ጓደኛ ሆኖ የተወነችው) አራተኛ ተሸላሚ አቶ ዳዊት እያዩ ( ደህንነት ) አምስተኛ ተሸላሚ አቶ ማንደፍሮ መንግስቱ (የደህንነት ሹፌር) ስድሰተኛ ተሸላሚ አቶ ሺበሺ ጌታቸው (ፖስተር ዲዛይነር) ሰባተኛ ተሸላሚ አቶ ዮናስ በመሆን ስጦታቸውን ተቀብለዋል ፡፡

ስጦታው ተሰጥቶ ሲያበቃም በምረቃው ላይ ከተገኙ እንግዶች አርቲስቶች አንዲሁም ከተሣታፊዎች መካከል አስተያየቶቻቸውን እንዲሰጡ እድሎች ቀርበው ገንቢ ሃሳብ ተሰጥቷል።

በመጨረሻም የበርገን ቅርጫፍ የኢሳት ድጋፍ ኮሚቴ ፊልሙ እንዲሰራ በማስተባብር ሂደት ውስጥ ከፍተኛ ልምድና ትምህርት አግኝቶታል በቀጣይም ከዚህ የተሻለ ስራ ይዞ ለመቅረብ በእቅዱ ውስጥ አስገብቶ እየሰራበት ይገኛል ፡፡ የሳአል ፍሬዎች ፊልም መነሻነት፡ ደፍረው ያልተነገሩ የወያኔ የአደባባይ ሚስጢሮች በሰፊው ለህዝብ ቀርበው ህዝቡ ፍርድ እንዲሰጥበት ማድረግ የሁሉም ኢትዮጵያዊ ግዴታ ነው ፡፡ ይህ ፊልም የፍርሃታችንን ድባብ አስወግዶ በሌላም ቦታ እንደዚህ የመሰሉ ስራዎች እንዲሰሩ ፈር ቀዳጅ ይሆናል ብለን ተስፋ እናደርጋለን ፡፡ የሳአል ፍሬዎች ቢልትና ቀልድ በበዛበት ዘመን ደፍሮ የተሰራ ኮስተር ያለ ፊልም ነው ፡፡ የማይነካውን ነክቶ ያሳየ መንገዱን ያመላከተ ባለን አቅም የተሰራ ፊልም ነው እኛ የምንችለውን አድርገናል ከዚህ በላይ የተሻሉ ስራዎች እንደሚሰሩ ተሰፋ እናደርጋለን ፡፡

የበርገን ቅርጫፍ ኢሳት ድጋፍ ሰጪ ኮሚቴ ህዝብ ግንኙነት

አቶ ዳዊት እያዩ

http://ethsat.com/video/esat-daily-news-amsterdam-march-30-2015-ethiopia/